# « ኀብላን አጭበርባሪው ጠጣ »

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

ማሳሰቢያ

ከአቤ ጉበኛ መጻሕፍት የአንዱን ርዕስ መዋስ የመረጥኩት፤ ያለንበትን ዘመን ገላጭ ሆኖ በማግኘቴ ነው ። ሃቀኛውና ደፋሩ አቤ ጉበኛ፤ በነበረበት ዘመን ለማንም ሳያጎበድድ በሰላ ብዕሩ የሚያስበውን ብሎ ሰው እንደሆነ፤ ሰው የሚያሰኘውን ሥራ ሠርቶ አልፏል ፡ ይህ ፈጣሪ ለጥቂቶች የሚቸረው ተሰጥኦ ነው ። እናም ቀናሁበት መንፈሳዊ የታናሽ ወንድምነት ቅናት !

መንደርደሪያ

ሰው ሰውነቱን ተገንዝቦ፤
ማን መሆኑን አስቦ፤
ማንነቱን ካልተረዳ፤
ማንም አይደል ምናምን ነው ባዶ የሆነ ጓዳ ።
ይለናል ተሰፋዬ ብርሃኑ **እንትን** በምትለው የምጥ ልጁ ።

መግቢያ

ጠመዝማዛ ነው መንገዱ !
ወደ ምርጫ ሲሄዱ !
በምርጫ ሕግ፤ እህ ! አንደበትህ፤ እህ ! ተቆልፎ፤
እጅና እግርህ፤ እህ ! በጠርናፊ፤ እህ ! ተጠርንፎ፤
ኮሮጆውም፤ እህ ! ቀድሞ በልቶ፤
በመለሰ ካርድ፤ እህ ! ሆዱ ሞልቶ፤
መረጥክ አሉህ፤ እህ ! ወያኔን፤
.......................... ። ቤት መምቻውን እናንተው አክሉበት፤
ጠመዝማዛ ነው መንገዱ !
ወደ ምርጫ ሲሄዱ !

በሰነ ምግባር ሰም አንደበት ዘግቶ፤ በመቀሌና በፓርላማ አሰፈራርቶ፤ በጳጳስ፤ በሼኪና በፓስተር አስገዝቶ፤ በጥያቄና መልስ ውኸንብር፤ በድጋፍ ሰልፍ ግርግር፤ በጠርናፊ ጠርንቆና አስጠርንቆ፤ ጢም ! አርጎ ኮሮጆ ሞልቶ፤ ምርጫው ሠላማዊና እንከን የለሽ ነው ብሎ መተርተር፤ በምርጫው ማግስት 99.6 በመቶ አሸነፍኩ ብሎ መፎከር፤ በምርጫ 97 ወቅት « ሥራ ፈት ቦዘኔ » ተብሎ እንዳልተሰደበ ዛሬ ለርካሽ የፓለቲካ

ፍጀታ « ጩዋው የአዲስ አበባ ሕዝብ » ተብሎ የአፍ ጬማ በሰባራ ገል በመስቀል አደባባይ ሲቀርብለት፤ « ከ97 ምርጫ ተምረን ብዙ ሠርተናል !» አሉን፤

አዎ ! ብዙ በጣም ብዙ የአፈና፤ የግድያ፤ የእስር፤ የሰብአዊ መብት ገፈፋ፤ የሬዲዮ ጣቢያዎች አመቃ ኸረ ምኑ ቅጡ ?! ብዙ እጅግ በጣም ብዙ በደል ሠርታችኋል ! የገረመን አለመካዳችሁ ነው፤ አልተለምደም ሆነብንና !!

ዝም ማለትን ስንመርጥ እንኳን ዝም የማያስብሉ ጉዶች በበዙባት አገራችን ኢትዮጵያ፤ ሳንወድ በግድ የኮረኮሩትን ያህል ያስቁናል ። ማን እንደሆኑ የተናገሩት ለጊዜው ቢዘነጋኝም፤ « የማይሆነው ሁሉ የሚሆንባት አገር » ያሉት ቁልጭ ብሎ ይታያል ።

ታዲያ ምን ገዷት አገራችን ፡ የሽፍታ ጠ/ ሚንስትር፤ የምሁር አጋሰስ፤ የነፍሰ ገዳይ ዳኛ፤ የሸማግሌ ቡጢኛ፤ የወጣት ልግመኛ፤ የጳጳስ ቂመኛ፤ የቄስ ቀማኛ፤ የአንድ ሌሊት ሃብታም፤ የወንድ......፤ የሴት......፤.....ሌላም ሌላም አፍርታለች ።

« ስኳር የተወደደው ገበሬው ስኳር መብላት ስለጀመረ ነው » አሉን ጠ/ ሚንስትራችን፤ ጉድ እኮ ነው! እድሜ ለወያኔ ! የኢትዮጵያ ገበሬ ማሩን ትቶ ስኳር መላስ ጀመረ ፡ አራዳነት ተማረ፤ (ነቄ ሆነ) ማለት ነው። ታምራት ላይኔ ልሶ ጨርሶት ነው አለማለታቸውም አግዜር ይስጣቸው ።

የሸማግሌ ጎረምሶች ድብድብ ፡ የሚፈነክተውን ፈንክቶ፤ ለወያኔ ጣት መጠቆሚና መሳቂያ አድርጓቸው፤ ያከብራቸውና ይተማመንባቸው የነበረውን ዜጋ አሳዝኖና አንገት አስደፍቶ፤ ካለፈ በኋላ፡አቶ መለስ « ወያኔ የመላእክት ስብስብ አይደለም » ባሉ ማግስት፤ በአንድላይ ጸልየው የማያውቁ፤ በአንድላይ የማይባርኩ፤ በአንድላይ የማይበሉና በአንድላይ የማያጠምቁ፤ ሃሰቱ ሰላሴዎች ክንፍ አውጥተው ሳይሆን በፓጀሮ በረው ከተፍ በማለት፤ በወያኔ አዛዥነት፤ በነሱ ሕሊና ሸጦ ለሆድ አድርነት፤ በአንድላይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወኔ ለመሰለብ ያደረጉትን ውግዘት ወይም እርግማን መሰል ንግግር ስንሰማ እውነትም ኢትዮጵያ የማይደረገው ሁሉ የሚደረግባት አገር ሆናለች ያሰኛል ።

በዘር፤ በጎሳና በሃይማኖት ፡ ተከፋፍለህ፤ በበሽታና በረሃብ እያለክ፤ አገርህ ለድንበር ዘለል ከበርቴ እየተቸበቸበች፤ ነፃነት፤ ፍትህ፤ እኩልነትና ዕድገት ተነፍገህ፤ እየተረገጥክና እየተራብክ፡ዝም ብለህ ተገዛ ብለው የሃይማኖት መሪ ተብዬዎች ገዝተውሃል ። ወገኖቼ ከእንግዲህስ ወዲያ ሃይማኖት ለምኔ ! አያሰኝም ?

ለመሆኑ በምርጫ 97 እና ከዚያ ወዲህ የዜጎች ደም በከንቱ ሲፈስ፤ ህግ ሲጣስ፤ ፍትህ ሲጓደል፤ ዜጋ ሲበደል፤ በሃሰት ሲወነጀል፤ ሌላው ቀርቶ ጨንቋቸው አራት ኪሎ በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተጠለሉ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በአጋዚ ወታደሮች እየተለቀሙ ሲወሰዱ በ10 ሜትር ርቀት ያሉ የሃይማኖት መሪ ጀሮ ዳባ ልበስ ያሉ ዛሬ ለግዝትና ለእርግማን ከየት ተገኙ ?! አቡነ ጴጥሮስ ሕዝባቸውን ለጣሊያን አትገዛ ብለው

በጣሊያን ጥይት ለሃቅ እንዳልወድቁ፤ የዘመነ ወያኔ ጳጳስ ብር ተንተርሰው በደም ምንጣፍ ላይ እየተረማመዱ የኢትዮጵያን ሕዝብ በባርነት ተገዛ በማለት ይገዝቱ ገቡ፤ ወይ ስምትተኛው ሺህ! እያሳየውና እያሰማው ጉድ የለ።

ምነው በዚህ ምስኪን ሕዝብ ላይ ሁሉም ተረባረቡበት፡ዝንቡም፤ ጨሉሌውም፤ ጆፌው፤ ጥንብ አንሳው፡ ኧረ ስንቱ!
ሰሞኑን፡ከዚህ ምርጫ ተብዬ ድራማ ወዲህ፡ የወያኔ ጀሌዎች፡ወንዱም ካደፈጠበት ብቅ ብሎ፡በድሃ ደም የደለበ ሻኛውን ሲያንጎባልል፤ ሴቷም ላባዋን ተነቅላ ጭር ካለችበት ማጀት ወታ፡ማስካካት ጀምራለች አሉ። «እነሱ ምን ያርጉ ከኛ ሰው ሲታጣ» አለ ልባሙ አቀንቃኝ፡፡ አዎ! እነሱ ምን ያርጉ፡የታዘዙትን ከማድረግ በቀር? ማሰቢያ ጭንቅላት ሳይሆን የቂቤ ቅል አይደል ተሸክመው የሚዞሩት። እናማ ባይገርመን አይደንቀንም።

መኢአድን በሾኬ ጠልፈው በኪስ ካስገቡ በኋላ፤ መድረኮችን ከምርጫ በኋላ እናስራችኋለን እያሉ በማዋከብ ላይ እንዳሉ፤ ያሰማሩት ጠርናፊ በተሳሳተ የሂሳብ ስሌት ልደቱን እንኳን ሳይቀር ጠርንፎ፤ በእንጀራ አባቱ አቶ መለስ «ልደቱን የነካ እጁ ይቆረጣል» ብለው ቃል ቢገቡለትም የፓርላማ ወንበር ሱሚ ሆኖ ቀረ። እናም ለማስመሰል ይንጫጫበት የነበረው የፓርላማ ወንበር ከሱ በላይ ለሚንጫጫ ተሸለመ። አብዛኛው ወገናችን ሲራብ ክምር ያህል ጭድ እየጎሰጎሰ ሸንት ቤት የሚኖላ እበት መጣል የለመደ ሆድ ባር ባር ማለቱ ስለማይቀር የሚጥሉለትን ፍርፋሪ ማነፍነፍ ጀምሯል።

«ጎብላን አጭበርባሪው ጠማም» በመስቀል አደባባይ የጨው ሃውልታቸውን ሲክቡ፤ ተቃዋሚዎች ዝምታን ከመረጡና ምርጫው ፍትሃዊና ሠላማዊ ነው ካሉ፤ የስልጣን እርጥባን ከወያኔ እንደሚመጸወቱ ተናግረዋል፤ አዎ ተናግረዋል! መለስን ያመነና ጉም የዘገነ አንድ ነውና፤ ማነህ ባለ ተራ! አልሰሜን ግባ በለው!!

በቸር ይግጠመን!!

ግንቦት 28 2002 ዓ.ም. (05/06/2010)